# "ጭስ የለውም እንጂ እሳቱስ አሪፍ ነው" (ክፍል አራት)

**ዮናስ** 3/14/13

በክፍል ሦስት ትርክቴ ዶ/ር መራራ ጉዲና ከኢትዮ ቻናል ጋር ያደረጉትን ቃለምልልስ መሰረት በማድረግ ስለማያውቁት ኢህአዴግና አብዮታዊ ዲሞክራሲ ኢ ዴሞክራሲያዊነት የዘረገፉትን ጥራዝ ነጠቅና ኢ.ምክንያታዊ አስተያየት ወደኋላ ተመልሼ በመሞገት በአራተኛ ክፍል መጣጥፌ ደግሞ የቅርብ ጊዜውን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታና የመልካም አስተዳደር አፈፃፀም ይገፍ ሙግቴን የምቀጥል እንደሆነ አውስቼ ነበር፡፡

በዚሁ መሰረት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚንስቴር በኩል ተዘጋጅቶ ለባለድርሻ አካላቶች ሁሉ ሰሞኑን ይፋ የሆነውንና ወይይት የተደረገበትን ሰነድ በዋናነት ከዶ/ር መራራ ጉዲና ቃለምልስ ጋር በንፅፅር የምመለከት ሲሆን እንደመንደርደሪያ ግን ዶ/ሩ ስለ አብዮታዊ ዲሞክራሲ "ቅሽምና" በተናገሩት ልክ ስለ ስርዓቱ ልማታዊ መስመርነትም እያወቁ እንዳላወቀ ለጥፈዋልና ስለስርዓቱ ልማታዊ መስመርነት ጥቂት ነገሮችን አነሳለሁ፡፡

ልማታዊ መንግሥታት በዓለማችን ከተከሰቱበት በተለይ ደግሞ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ባሉት ዓመታት የተፈጠሩት ልማታዊ መንግስታት የምዕራቡ ዓለም በተለይም የኒዮ ሊበራል ርዕዮት አራማጅ የሆኑት ተቋማት የሰጧቸውን የኢኮኖሚ ምክርነትና መመሪያዎች ቸል ብለው በራሳቸው ልማታዊ አቅጣጫ በመጓዝ ከዝቅተኛ ደረጃ ተነስተው በአርባና ሃምሳ ዓመታት የበለፀገውን ዓለም ጎራ መቀላቀል የቻሉ ናቸው፡፡ ይህ የልማታዊ መንግሥት አቅጣጫን በመከተል የመጣ ለውጥ ለማንኛውም ያልበለፀገ አገር ከፍተኛ ትምህርት የሚሰጥ ቢሆንም የምዕራቡ ዓለም ሚዲያዎች ፈጣን እድገት ያስመዘገቡ የምስራቅ እስያ አገሮችን ተሞክሮ አንድም ባለማቅረብ አሊያም እያውገረገሩ ከፊል እውነታዎችን ከከፊል ውሸቶች ጋር ቀላቅለው በማቅረብ ሊያዳፍኑት ሞክረዋል፡፡ የምስራቅ እስያ አገሮች ልማት ገዝፎ ሲወጣም ጥቂት የማይባሉ የምዕራቡ ዓለም ሚዲያዎችና ምሁራን፣በእኛም ሃገር የሚገኙ አንዳንድ የፕሬስ ውጤቶች ከነዶክተር መራራ ጋር በመጣመር የልማታዊ መንግስታቱን ጥረትና ተነሳሽነት እያኮሰሱና የምዕራባውያንን በጎ አድራጊነት እያጎሉ በማቅረብ ተጠምደዋል።

ይህም ሆኖ በጊዜ ሂደትና ራሳቸው ልማታዊ መንግስታቱ ስራቸውን ማሳየት መቻላቸውን ተከትሎ የዓለም ህዝቦች ለምስራቅ እስያ አገሮች የፈጣን እድገት ጉዞ እውቅና መስጠት በመጀመራቸው የምዕራቡ ዓለም ሚዲያዎች በዋነኛነት አገዛዞቹ በነበራቸው ኢ ዲሞክራሲያዊ ገፅታ ላይ ተንጠላጥለው ዘመቻ ሲያካሂዱ ቆይተዋል፡፡ በተለይ ደግሞ አሁን ቻይና የዓለምን የሃይል ሚዛን በእርግጠኝነት በሚቀይር ደረጃ ልማታዊ የፖለቲካ ኢኮኖሚ መገንባቷን ተከትሎ ኢ-

ዴሞክታሲያዊ ወይም አምባገነናዊ ልማታዊ መንግሥት /Authoritarian Development State/ የሚል ስያሜ አስቀድመው ቻይናዊያን በማስመዝገብ ላይ ያሉትን ድል ጥላሸት መቀባት መርጠዋል፡፡

በዓለማችን የኒዮ ሊበራል ኃይሉ መነሻና መድረሻ የኒዮ ሊበራል የፖለቲካ ኢኮኖሚ ማስፋፋት በሆነበት በዚህ ዘመን ኢትዮጵያ እንደማንኛውም አፍሪካዊ አገር አስተሳሰቡን በግድ እንድትጋት ለማድረግ የተካሄደባትን ጫና በመቋቋም የራሷን ነፃ መንገድ ከመምረጧ ጋር ተያይዞ የኒዮ ሊበራል ሚዲያውና የዜሮ ድምር ስብስቡ የሃገሬ ተቃዋሚ የፕሮፖጋንዳ ሰለባ እስከመሆን ደርሳለች፡፡ ለእነ ዶ/ር መራራ ዛሬ ቢመስልም ኢትዮጵያ ከኒዮ ሊበራል መመሪያዎች አፈንግጣ በራሷ ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ አቅጣጫ መንገዝ የመረጠችው ከደርግ ውድቀት ማግስት ነው፡፡ ምንም እንኳን ልማታዊ አቅጣጫዋን ይበልጥ በጠራ መሰረት ላይ የገነባችው ከተሃድሶ ንቅናቄው በኋላ ቢሆንም የኒዮ ሊበራል መመሪያዎች እንዳይጫኑባት አሻፈረኝ ማለት የጀመረችው ግን ከደርግ ውድቀት ማግስት ነው፡፡

በሰማንያዎቹ መጀመሪያ ላይ ከአበዳሪ ተቋማት ጋር በተካሄዱት ድርድሮች ኢትዮጵያም እንደማንኛውም አፍሪካዊ አገር ፈጣን ሊበራላይዜሽንና ፕራይቬታይዜሽን እንደአቅጣጫ ተግባራዊ እንዲሆንባትና የመንግስትን አቅም የማዳከም አቅጣጫ እንድትከተል ከባድ ግፊት ደርሶባት ነበር፡፡ መሬትን ከመንግስት ወደ ግል ይዞታ እንድታሻግርና በገበያ የሚቸረቸር ሸቀጥ እንዲሆን፣ የኢኮኖሚው ከፍታ ነጥቦችና ቢያንስ አሁን ባለንበት ደረጃ በግሉ ዘርፉ ሊሸፈኑ የማይችሉ ዋነኛና ወሳኝ የመሰረተ ልማት አውታር የሆኑትን ትልልቅ ተቋማትን ጨምሮ በመንግሥት እጅ ያሉ የኢኮኖሚ ተቋማትን ሁሉ በፍጥነትና በርካሽ ወደ ግል እንድታዘዋውር፣ የመንግሥትን የስራ አቅም በተለይ የሰው ኃይሉን በማራገፍ እንድታዳክም ወዘተ ከብድር ቅድመ ሁኔታ ጋር የተያያዙ ኒዮ ሊበራል አቅጣጫዎችን እንድትከተልም ከባድ ጫና ተደርጎባት ነበር፡፡ መንግሥት ከሁሉ በማስቀደም የእዝ ኢኮኖሚን ለማፍረስና በገበያ ኢኮኖሚ ለመተካት የሚያስችል የራሱን አገር በቀል ፕሮግራም አዘጋጅቶ ስለነበርና ከአበዳሪ ድርጅቶች ጋር የሚያደርገውን ድርድር ሁሉ በዚህ ፕሮግራም በመመራት ሊያካሄድ በመቻሉ ከገበያ አክራሪነት ርዕዮተ ዓለም በመነሳት የቀረቡለትን መመሪያዎች ሁሉ ውድቅ ማድረግን መርጧል፡፡ በሂደት ደግሞ የራሱን ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ የፖለሪካ ኢኮኖሚ ግንባታ አቅጣጫ ነድፎ ይህንኑ ተግባራዊ በማድረግ ለውጥ በማምጣት ላይ እንዳለ የእነ ዶ/ር ስብስቦች ያውቁታል፡፡ ለውጡም ልማታዊ ብቻ ሳይሆን ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ይዘት ያለው ነው፡፡

ኢትዮጵያ በለውጥና እድገት አቅጣጫ መራመድ ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ ከኒዮ ሊበራል የገበያ አክራሪነት በመሰረቱ የተለየ አቅጣጫ የመረጠች አገር መሆኗ ከዓለም አቀፉ የገበያ አክራሪ

ኃይልና የእርሱም አንድ ክንፍ ከሆነው የኒዮሊበራል ሚዲያና የዜሮ ድምር ስብስቡ ጋር በርዕዮተ ዓለማዊ ደረጃ ሊፈረጅ የሚችል ልዩነትና ትግል ውስጥ ገብታለች፡፡ ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ፍላጎት ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አቅጣጫን በራሷ አገራዊ አጥር ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ እንጂ ይህንኑ ኤክስፖርት ማድረግ ባይሆንም ገና ለገና ከተሳካላት መልካም ጎዳና ለሚያማትሩ ሁሉ አብነት ሆና ትታይ ይሆናል ከሚል ስጋት በመነጨ የኒዮ ሊበራል ሚዲያውና የቀለም አብዮት አራማጆች የጥቃት ሰለባ ሆና ቆይታለች፡፡

በዚህ መሰረት ነው እንግዲህ እነ ዶ/ር መራራ እና ዓለም አቀፉ የገበያ አክራሪ ኃይል በኢትዮጵያ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ላይ በታሰበበት አኳኋን የማጥላላት ዘመቻ የከፈቱት፡፡ ዘመቻው በተለያዩ ወቅቶች የተለያየ መልክ ይዞ የሚካሄድ ነው፡፡ በለውጡ ማግስት ዘመቻው ሲጀመር የነበረው መልክ “በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ኮሚኒስት ነው፣ ሶሻሊስት ቅኝት አለው ወዘተ . . .” የሚል ነበር፡፡ ጀማሪ የነበረውን የፌደራል ስርዓትም እንደጎሳ ፖለቲካ ፈርጆ ማጥላላት የተለመደ ነበር፡፡ በሂደት ዴሞክራሲውና ፌዴራላዊ ስርዓቱ እየጎለበተ ሲሄድ ደግሞ የተለያዩ አጋጣሚዎችን በመጠቀም ኢትዮጵያን የማጥላላትና ስርዓቱን በዓለም ማህብረሰብ ፊት ጥላሸት ቀብቶ ማሳየት የተለመደ ሆነ፡፡ በምርጫ 97 በተፈጠረው አጋጣሚ አክራሪው ኃይልና የሚዲያ ኢንዱስትሪው የኢፌዲሪ መንግሥት የሰብዓዊ መብት ጥሰት የሚያካሄድ እንደሆነ አስመስለው ማቅረብን ስራዬ ብለው አሁን ድረስ ገፍተውበታል፡፡

በአገራችን የሚገነባው ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ከውስጥና ከውጭ ተፃራሪ ኃይሎች ግምት ውጭ ፈጣን ልማትና የህዝብን የኑሮ ደረጃ መሻሻል ሲያስከትልና ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓቱም የተሻለ ፖለቲካዊ ማዕቀፍ ሆኖ የግልና የቡድን መብቶችን ሲያስከብር ደግሞ ዘመቻው ይበልጥ እየተጧጧፈ ሊሄድ ችሏል፡፡

በዚህ ረገድ የሚካሄደው ዘመቻ የተለያዩ ገፅታዎች ያሉትና ከአገር ውስጥ የተቃውሞ ፖለቲካ ጋር በተመጋጋቢነት የሚካሄድ ነው፡፡ የዶ/ር መራራ ቃለ ምልልስም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እንደ ሂዩማን ራይትስ ዎች፣ አምንሲቲ ኢንተርናሽናል፣ ሲፒጄና ግዙፍ የኒዮ ሊበራል ሚዲያዎች ከተቃዋሚው ሃይል ጋር እጅና ጓንት ሆነው የመሬት ወረራ አፈታሪክ፣ የፀረ ሽብር ህግ፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ህግ፣ የፕሬስ ህግ ወዘተ ላይ በማተኮር የሚያካሂዱት ዘመቻ አካል ነው፡፡ ድርቅን የመከላከልና በራሳቸው በለጋሾች ሳይቀር የተመሰከረለት ፍትሃዊ የእርዳታ እደላ ስርአታችንና ህዝቦችን ከድህነትና ኋላቀርነት ለማላቀቅ የሚካሄዱ የውሃ ሀብት ልማቶችና የፈቃደኝነት ሰፈራ ፕሮግራሞች ሁሉ ለዘመቻው በግብዓትነት እንዲያገለገሉ ከመደረግ አላመለጡም፡፡ ይህም ሆኖ በሁሉም የዘመቻ ማቴሪያሎች ዘንድ ጎልቶ እንዲወጣ የሚፈልገው የሰብዓዊ መብት ጥሰት ወይም የኢፌዲሪ መንግሥት ለሰው ልጆች መብት ግድየለሽ ነው የሚል

መልዕክት ነው፡፡ በዚህም አድርገው በልማቱና በዴሞክሲያዊ ሰርዓት ግንባታው መስክ የመጣውን ድል ለመድፈቅና እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የልማት ስኬታችን እንዳይታይ ለማድረግ ሲሞክሩ ቆይተዋል፡፡

የልማት ስኬቶቻችን ከማንም የአፈና ሙከራ ባሻገር በዓለም አቀፍ ደረጃ መታየትና እውቅና ማግኘት ሲጀምሩ ደግሞ የመጨረሻ አማራጭ ተደርጎ እየተወሰደ ያለው ስርዓቱ ዲሞክራሲያዊና ልማታዊ ስርዓት ሆኖ እንዳይታይ ማድረግ ነው፡፡ ለዚህ ይበጃል ተብሎ የተመረጠው የገፀ ባህሪ ስያሜ ደግሞ አምባገነናዊ ልማታዊ መንግስት/ Authoritarian Development State / የሚል ሆኗል፡፡ ይህ ስያሜ በተለይ ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ ጎልቶ እንዲወጣና የእለት ተዕለት መጠቀሚያ እንዲሆን ለማድረግ የሚካሄደውን ጥረት ስንመለከት የምናገኘው የሳንቲሙ ሌላኛው ገፅታ ኢትዮጵያ ማንም ሊክደው በማይችለው ሁኔታ የአፍሪካ "ነብር ኢኮኖሚ" ባለቤት ተብላ መቀጠሏ ነው፡፡ ይህም የኢትዮጵያ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ለውጥ ይበልጥ እውቅና እያገኘ በሄደ ቁጥር በአፍሪካና በሌሎች ታዳጊ አገሮች ላይ የሚያሳድረው በጎ ተፅዕኖ ግዙፍ ከመሆኑና በአክራሪ የገበያ ስርዓት አራማጆችና የአቋራጭ ስልጣን ፈላጊዎች ላይ የፈጠረው ስጋት ትልቅ ከመሆኑ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው፡፡

ዓለም አቀፋዊው የኒዮሊበራል ኃይል በኢትዮጵያ ላይ የሚያካሂደው ዘመቻ ስፋቱና ጥልቀቱ እየጨመረ መምጣቱና የሚንቀሳቀስባቸው አጀንዳዎችም በዋነኛነት ከፖለሪካዊ ኢኮኖሚ ጥቅሞች የፈለቀና ከእነዚህም ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው፡፡ በዘመናችን ኒዮ ሊበራል ኃይሉ የሚቆሰቁሳቸው የቀለም አብዮቶች በዋነኛነት የትልልቁን ባለሃብት ጥቅሞች ለማስከበር ያለሙ ናቸው፡፡ ይህ መሰረታዊ ሃቅ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀለም አብዮቶቹን በማቀድና በማስፈፀም ረገድ የኒዮ ሊበራሊዝም አራማጅ የሆኑት መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እና ኒዮ ሊበራል ሚዲያው በተናጠልና በቅንጅት ግንባር ቀደም ተዋናዮች ሆነው ተንቀሳቅሰዋል በመንቀሳቀስም ላይ ይገኛሉ፡፡

ኒዮ ሊበራል ሚዲያው የቀለም አብዮቶችን ከማቀጣጠል አኳያ የሚጫወተው ሚና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ የመጣ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ የቀለም አብዮቱ በሚካሄድበት አገር ከሚገኙ የውጭ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ጥገኛ የሲቪል ማህበረሰቦች ጋር በመረጃና በምስል እየተመጋገበ ነገሮችን ከትክክለኛ ምጣኔያቸው በላይ እያጋነነ በማቅረብ የተጀመሩ ንቅናቄዎች እንዲስፋፉ ያደርጋል፡፡ ለዚህም ሲል አብዛኛውን ጊዜ ከምርጫ ጋር የተያያዙ ውዝግቦችን በግብዓትነት ይጠቀምባቸዋል፡፡ በመሆኑም እነዚሁ ድሃና ታዳጊ አገሮች ከምርጫ ጋር የተያያዘ ወይም አንዳች ዓይነት ግብታዊ መነሳሳትና ግጭት ከተከሰተባቸው ይህንኑ እንደ መግቢያ በመጠቀም ሚዲያውና ፓርቲዎቹ በተመረጠ መረጃ ሰፊ አቅርቦትና ሆን ብሎ በሚካሄድ የማደናገር ዘመቻ ይጠመዳሉ፡፡ ይህን ከማድረግ አኳያም ዘመናዊው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አውታር መስፋፋት የፈጠረላቸውን እድል በሰፊው ይጠቀሙበታል፡፡ ኢንተርኔት እንደ ፌስቡክና ትዊተር የመሳሰሉ ማህበራዊ

ሚዲያዎች፣ በሞባይል ስልክ ቴክስትና ምስል በቀላሉ የማስተላለፍ እድሎች ሁሉ የቀለም አብዮቱ ማስፈፀሚያ መሳሪያዎች ተደረገው ይወሰዳሉ፡፡ እነ ዶ/ር መራራና ስብስባቸውም እያደረገ ያለው ይህንኑ ነው ።እስኪ ደግሞ አሁን ከእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ የሁለት አመታት ጉዞ በመልካም አስተዳደርና በዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ዘርፍ ያለውን አፈጻጸም በመጠኑ እንመልከት፡-

## የፍትህ ስርአት ማሻሻያ

የፍትህ ስርዓቱን ባለሙያዎች አቅም የሰው ሀብትን አቅም ማጎልበት ለማጎልበት የአጨርና የረጅም ጊዜ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ በዚህም መሰረት ከ5 ሽህ 642 በላይ ከፍተኛ ባለሙያዎች አግባብ ያለው ስልጠና፣ ጠበቃዎችን ጨምሮ  ከ7 ሽህ 249 በላይ ለሆኑ  ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች እንዲሁ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም የፍትህ ስርዓቱን የሰው ሃይል ለማጎልበት 18 ጥናቶች የተጠናቀቁ ሲሆን ሌሎች 15 ጥናቶች በሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡

አሁን ያለው የፍትህ ስርዓት ሁሉን አቀፍ አሰራር እንዲከተል መደረጉ ወንጀልን ለመዋጋት እና ለመከላከል የተሻለ ሥራ እንዲሰራ፣ የሞትን ቅጣት ለመቀነስና የምስክሮችን ደህንነት በማስጠበቅ፣ በአጭር ጊዜ የፍትህ ሂደቶች የሚጠናቀቁበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከ96 ሽህ 165 በላይ የክስ መዝገቦች ታይተዋል፡፡ ይህም ካለፈው አመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ5 ሽህ 518 መዝገቦች የበለጠ ነው፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ተለዋጭ ቀጠሮዎች እና የይግባኝ መዝገቦች ከ90 በመቶ  ወደ 97.2  በመቶ ተመንድጓል፡፡ በፌደራልም ሆነ ክልል በሚገኙ የፍትህ አካላት በ2010/11  አማካይ የፍትህ አሰጣጥ  ርዝማኔ ጊዜ ከ45 ቀናት እስከ ሁለት ወራት ይወስድ ከነበረበት  አሁን ወደ  ከ 22 ቀናት እስከ አንድ ወር ባለ ጊዜ ቀንሷል፡፡

የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ከሀገሪቷ ህገ መንግሥት እና ከዓለም አቀፍ ህጎች በተስማማ መንገድ  በዚህ በእድገትና ትራንስፎርሜሽኑ ወቅት ተያያዥ ህጎች  መውጣታቸው ይታወቃል፡፡ ከነዚህም ውስጥ 6 የሚሆኑት ህጎች ደንቦች እና የአፈፃፀም ስርዓቶች  ረቀው ፀድቀዋል፡፡ በአጠቃላይ 134 ህጎች ተረቀዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ   ህገ መንግስቱንና  ሌሎች ህጎችን በተመለከተ የዜጎችን ንቃተ ህሊና ለማሳደግ ጥረት ተደርጓል፡፡   ግልፅነትንና ተጠያቂነትን በፍትህ ስርዓቱ ውስጥ ለማስረፅ የተለያዩ ህጎች ደንቦችና መመሪያዎች ለማውጣት በታቀደው መሰረት 46 የሚሆኑቱ ጸድቀው በስራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ ተቃውሞ የማቅረቢያ ዘዴዎችም እንዲሁ ተዘጋጅተው ስራ ላይ ውለዋል፡፡

የፍትህ አገልግሎቱን ለሰፊው ህዝብ ተደራሽ ለማድረግ የአገልግሎት ማዕከሎችን የማሰፋፋት ስራ የተሰራ ሲሆን ይህም አገልግሎቱን በስፋትና በጥራት ተደራሽ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ የዳኞችና የአቃብያነ ህጎች ቁጥርም እንዲጨምር ተደርጓል፡፡ ተጠሪጣሪዎች እና ባለጉዳዮች ባሉበት   ቦታ ሆነው የፍትህ ሂደቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችለውን ቪዲዮ ኮንፍረንሲንግ  ለመጠቀም የሚያስችል ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎችም በስፋት በዚሁ አመት ስራ ላይ ውለዋል፡፡

በእድገትና ትራንስፎርሜሽኑ እቅድ የህገ ታራሚዎች አያያዝና ጥበቃ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ጥረት እንደተረገ የሚያወሳው ሪፖርት ታራሚዎች የፍርድ ጊዜያቸውን ጨርሰው ሲወጡ ጠቃሚ ዜጋ እንዲሆኑ ለማስቻል የሙያ ማሻሻያ ስልጠናን በዚሁ በ2011/12 እንዲያገኙ መደረጉንም ያብራራል፡፡

መቻቻልን የሚያበረታቱ ባህሎችን እና ማህበራዊ እሴቶችን በመገንባት ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት በታቀደው መሰረት 729 የሰላም ኮሚቴዎች እና ክለቦች ተቋቁመዋል፡፡ በህይማኖት ተቋማት መካከልም መግባባት ህብረት እና መከባበር እንዲሰፍን የማይናቅ ስራ ተሰርቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከተለያዩ ቦታዎች ለመጡ ከ144 ሽህ 732 ለሚበልጡ ተሳታፊዎች ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡

ለግጭት ተጋላጭ በሆኑ ቦታዎችን በመለየት ግጭቶችን በዘላቂነት ለመፍታት የተለያዩ ማኑዋሎች የተዘጋጁ ሲሆን ከ780 የፍትህ ሰላም እና ደህንነት ክፍል የበላይ አመራሮች ጋር ምክክር እና ወይይት ተደርጓል፡፡ ከ6 ሽህ 439 በላይ ከሆኑ ጎልማሶች ሴቶችና ወጣቶች ተወካዮች ጋርም ስለ ሰላምና ደህንነት ምስረታ ውይይት ተካሂዷል፡፡ በኢኮኖሚና ፖለቲካ የተጠናቀረ ማህበረሰብ አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብ ለማቋቋም እንዲሁም በተለያዩ ክልሎች የሚገኙትን የብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦችን የእርስ በርስ ግንኙነት ለማጠናከር የተለያዩ ስራዎች መሰራታቸው የሚገልጸው ጥናት 6ኛው የብሔር ብሄረሰቦች ቀን በትግራይ ክልላዊ መንግስት ዋና ከተማ መቀሌ በሲምፖዚየምና የባህል ትርዒት በደመቀ ሁኔታ መከበሩ ፍሬ ያፈራ መልዕክት እንዲተላለፍበት ያስቻለ ሲሆን የብሄራዊ ባንዲራ ቀን እንዲሁም አለም አቀፍ የዲሞክራሲ ቀን መከበሩም በተመሳሳይ የህዝቡን ህገ መንግሥታዊ ግንዛቤ የማስፋትና ተጠቃሚነቱንም የማረጋገጡ ጥረት እየተሳካ መሆኑን አመላክቷል፡፡

በተመረጡ የፌደራል ተቋማት እና ክልላዊ መንግሥቶች ላይ በተደረገ ግምገማ እና ክትትል ህጋዊ አወቃቀር ያለው የፍትህብሄር እና የአንድ የምጣኔ ሀብት (economy ) እና የፖለቲካዊ ምጣኔ ሀብት(political economy ) እንዲፈጠር አድርጓል፡፡ በተጨማሪም በሀረር፣ ሶማሌ ፡ደብብህ እንዲሁም በኦሮሚያ ክልሎች እና በሁለቱ የፌደራል ከተሞች በተደረገ ክትትል(ግምገማ) የተገኙት መረጃዎች ለወደፊቱ አሰራር ጠቃሚ ሆነው መገኘታቸውም ተመልክቷል፡፡

ፍትሀዊ የበጀት ክፍፍልን ለማድረግ ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ፣ የዋና ኦዲተር ቢሮ፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሚኒስትር መ/ቤቶች እና ክልላዊ መንግስቶች ጋር በመተባበር የክልሎች ገቢ፣ ወጪና የበጀት አጠቃቀምን የተመለከተ የስራ ግምገማ ተደርጓል፡፡ ይህ ከተጠናቀቀ በኋላ አዲሱ የፌደራል የበጀት ድልድል ቀመር በተሻለና ሁሉን አቀፍ በሆነ ፍትሃዊ እና ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ክልላዊ መንግስቶች ግምት ውስጥ ያስገባ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ የአዲሱ ቀመር አሰራር ከጅምሩ ማለትም ከሃሳቡ ጽንሰትና ዝግጅት እስከ አፈጻጸሙ ድረስ በየደረጃው ያሉ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ያሳተፈ እና በጋራ ስምምነት ላይ ተመስርቶ ተቀባይነት ያገኘ ነው፡፡ ሁሉም የዚህ ቀመር አካላት ከመጀመሪያው ጀምሮ የነቃ ተሳትፎ ያደረጉበት እንዲሁም ስልጠና እንዲያገኙ የተደረገበት ነው፡፡

ህገ ማውጣት አንዱ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስልጣንና ሀላፊነት መሆኑ ይታወቃል፡፡ የተለያዩ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ያካተቱ ሰነዶች ከመንግስት ወደ ህግ አውጪው የቀረቡ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ እኤአ በ2011/12 ላይ 50 አዋጆች እንዲፀድቁ ተደርጓል፡፡ ምክር ቤቱ በዚሁ አመት የግማሽ ቀን የውይይት መድረክ አዘጋጅቶ ከመንግስት ህግ አስፈፃሚ አካላት ጋር ተወያይቶ ስምምነት ላይ የደረሰ ሲሆን ሌላው ምክር ቤቱ በቋሚ ኮሚቴ አባላቱ አማካኝነት የመንግስት አካላት የሥራ አፈፃፀም እቅድ ሪፖርት እንዲያቀርቡና አስፈላጊም ሆኖ የተገኙትን በግል ቀርበው ለምክር ቤቱ ወይም ለቋሚ ኮሚቴው እንዲያቀርቡ ተደርገዋል፡፡ በዚህም መሰረት በ206 የሥራ አፈፃፀሞች ላይ ሰፊ ውይይት ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የምክር

ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ ሰፊ የክትትል ስራ ሰርቷል፡፡ እነዚህም 88 ጊዜ በመስክ ጉብኝት ወጥቶ በመመልከት እና የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የተከናወኑ የክትትልና የቁጥጥር ስራዎች ናቸው።

በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን (አራት የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎችን ጨምሮ) በመጠቀም የተለያዩ የዜጎችን ህገ መንግስታዊና ፌደራላዊ ግንዛቤ ለማሳደግ ተሞክሯል፡፡ የሬዲዮ ጥያቄና መልስ ዝግጅቶችን (ጥቂቶችን ለመጥቀስ) በአማርኛ ኦሮሚኛና ትግሪኛ እና ሌሎችም ቋንቋዎች በክልል ሬዲዩ ጣቢያዎች ጭምር ተላልፈዋል፡፡ በአጠቃላይ በ150 የተለያዩ ፕሮግራሞች በተለያዩ ቋንቋዎች እንዲሰራጩ ተደርጓል፡፡ በበጀት አመቱ 40 ፕሮግራሞች በኢትዮጲያ ቴሌቪዥን መተላለፋቸው መንግስት ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ የሰጠውን ልዩ ትኩረት የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ህግመንግስቱ በተለያዩ ቋንቋዎች ታትሞ ተሰራጭቷል፡፡ እንደዚሁም ከ14ሽህ 20 በላይ በመሰረታዊ የፌደራላዊ እና ህገመንግስታዊ ንድፈ ሃሳቦች ላይ ያተኮረ የስልጠና ማንዋል በአማርኛ ትግሪኛ እና ኦሮሚኛ ቋንቋዎች ተዘጋጅተው ወደ ተለያዩ የፌደራል ተቋማትና ክልላዊ መንግስታቶች ተሰራጭቷል፡፡

የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ እስትራቴጂያዊ አቅጣጫ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የህዝብ ተወካዮች(ህግ አውጪው) ግልፅነት ያላቸው አዋጆችን እንዲያወጣ የሚረዳ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የህግ ማውጣት እና ክትትል ስራን በብቃት ለማከናወን የምክር ቤቶችን ቋሚ ኮሚቴ አባላት አቅም ለማጎልበት ጥረት ተደርጓል፡፡

በተመሳሳይም የምክር ቤቱን አባላት የመሪነት እና ችግር የመፍታት ክህሎት ለማሳደግና የተሻለ የስራ ልምድ እንዲያዳብሩ የተዘጋጁት ወርክሾፖችና ስልጠናዎች ህገ መንግስት የመተርጎም፣ የክልሎች የድጎማ ቀመርን፣ የብሄር እና ብሄረሰቦችን መብት፣ የመሪነት ክህሎትን እና የመሳሰሉትን ለመተግበር የሚያስችሉ የተለያዩ ሥልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡

በዜጎች ውስጥ የሰብአዊ መብቶችን ለማስፈን ዲሞክራሲያዊ ተቋማትን እና ህግ አስፈፃሚ አካላትን አቅም ለማጎልበት የተለያዩ የአጭር ጊዜ ስልጠናዎችና የፓናል ውይይቶች ከኦሮሚያ፣አማራ፣ ደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ፣ትግራይ፣ሐረሪ እና ሶማሌ ክልላዊ መንግስቶች ከመጡ ተሳታፊዎች ጋር ተደርጓል፡፡ ከ2 ሽህ 218 በላይ የሆኑ የመከላከያ ሰራዊት፣ የፌደራል እና ክልላዊ ፖሊስ ኮሚሽን፣ የፌደራልና ክልላዊ ማረሚያ ቤቶች አባላት፣ ዳኞች፣አቃብያነ ህጎች እና የተለያዩ የህግ አስፈፃሚ አካላት ተወካዮች፣ የአስተዳደር ሰራተኞች ስልጠና እንዲያገኙ መደረጉን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ የሰብአዊ መብቶች አጠባበቅ የስራ ዕቅድ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ረቂቅ አዘጋጅታለች፡፡ ከመፅደቁም በፊት ከባለድርሻ አካላት ጋር ቀጣይ ውይይት የሚደረግበት ይሆናል፡፡

ቁጥጥርና ክትትልን በተመለከተ በሰብአዊ መብቶች ጥበቃ እና የኮሚሽኑን ተደራሽነት ለማስፋት ስድስት አዲስ ቅርንጫፍ ቢሮዎች በመቀሌ ፣ባህርዳር ፣ጂማ፣ ጋምቤላ፣ ሀዋሳ እና ጂጂጋ ባለፈው በጀት አመት ተከፍተው ሙሉ በሙሉ ስራ ላይ ውለዋል፡፡

ከአመት በፊት በተከፈቱ ህጋዊ የድጋፍ ማዕከሎች (Legal Aid Centers) ኮሚሽኑ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና ከማህበረሰባዊ ተቋማት ጋር በመሆን ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት

በመስጠት ላይ ሲሆን በዚሁ መሰረት 7 ሽህ 872 ዜጎች የዚሁ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ ተጨማሪ 102 የህጋዊ ድጋፍ ማዕከሎች ተከፍተው የተለያዩ ድርጅቶች ከኮሚሽኑ እና ከማዕከሎቹ ጋር አብረው እየሰሩ ነው፡፡ ኮሚሽኑ ከተዘረዘሩት በተጨማሪም የስራ እና የቁጥጥር ማንዋል በበጀት አመቱ አዘጋጅቷል ፡፡ በዚሁ የሰብአዊ መብት አጠባበቅ ዙሪያ እና በመብቶች መሰረታዊነት እና ትግበራቸው ላይ በርከት ያሉ ውይይቶች መደረጋቸውና ስልጠናዎች መሰጠታቸው ለእቅዱ ስኬት ከፍተኛ ጥቅም ማስገኘታቸውን ነው ጥናቱ ያመላከተው፡፡

በዚህ እቅድ ዘመን እና አፈጻጸም ሂደት ላይ ዋናው ችግር ኪራይ ሰብሳቢነት መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለዚህም ይህንን የዕድገት ማነቆ ለማጥፋት ይቻል ዘንድ የችግሩን ስር ለመለየት የተሞከረ ሲሆን በተያያዥም ይህንኑ ለመቆጣጠር የተለያዩ የመከላከልና መቆጣጠር ሰራዎች ተሰርተዋል፡፡ ከእነዚህ የኪራይ ሰብሳቢነት ተግባራት ውስጥ ስልጣንን ተጠቅሞ ያለአግባብ ጥቅም ለማካበት በሚደረግ ተገቢ ያልሆነ እንቅስቃሴ ወደ ሙስና የሚመራ በመሆኑ ጠንከር ያለ የቁጥጥርና መከላከል ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

ሙስናን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የተቋሞች አቀምን ማጎልበት፤ በጥራት በብቃት እና ግልፅነት በሰፈነበት አግባብ ዲሞክራሲያዊ ስርዓትን ለማሰፈን የስነ ምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽን በተለያዩ የቅስቀሳ ጽሁፎች፣ሕዝባዊ የውይይት መድረኮች፣በሚዲያዎችና በየደረጃው በሚሰጡ ሥልጠናዎች በመታገዝ የዜጎችን ግንዛቤ በማሳደግና በጸረ ሙስና ትግሉ በባለቤትነት መንፈስ በማሳተፍ ረገድ ትልቅ ሚና በመጫዎት ላይ ይገኛል።

እነዚህ እንግዲህ ከብዙ በጥቂቱ የተመለከቱ የመልካም አስተዳደርና የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ የሁለት ዓመታት ክንውኖች ናቸው። መንግስት ለጉዳዩ ካለው ቁርጠኝነትና ከሕዝቡ ያላሰለሰ ጥረት አኳያ በነዚህ ዓመታት ውስጥ ይህን መፈጸም ከተቻለ በቀጣይ የተሻለ ደረጃ ላይ መድረስ እንደምንችል ይህ ስኬት ግልጽ አመላካች ነው።